**የተከበሩ አቶ ያለው አባተ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ ምክትል አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

1. ከሁሉም በማስቀደም በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና እንቀፅ 10/2 መሰረት የዋና ኦዲተር መ/ቤት የክልሉ መንግስት ተቋማትና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ም/ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ ውስጥ እንዲሰሩ ለተወሰኑት ስራዎች በሚገባ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለምክር ቤቱ እንደሚያቀርብ በሚደነግገው መሰረት ይህን ሪፖርት ለተከበረው ም/ቤት እንዳቀርብ ዕድሉን በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡
2. በመሆኑም መ/ቤቱ በኢንትሪም ኦዲት የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ከጥር 1/2005 እስከ ታህሳስ 30/2006 ዓ.ም የ170 መ/ቤቶችን የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ152 መ/ቤቶችን (89%) አከናውኗል፡፡ በዚህ ጉባኤ የቀረበው በ2005/2006 በጀት ዓመት የተከናወነ የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ውጤትን የሚያሳይ ሪፖርት ብቻ ነው፡፡
3. በ2005/2006 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 34(22%)፣በዞን 8(5%)፣በከተማ አስተዳደሮች 30(20%) ቀሪዎች 80(53%) በወረዳዎች ናቸው፡፡ኦዲቱ የተከናወነው የክልሉን ያልተማከለ አወቃቀርና የበጀት ፍሰትን ተከትሎ ሲሆን አካሄዱም ስጋትን(Risk based Approch) መሠረት ያደረገ፣ የበጀት መጠንና የስራ ውስብስብነትን ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን በዚህም ለ2005 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀው ጠቅላላ የክልሉ በጀት ብር 17,264,356,899.00 ላይ ብር 10,325,723,393.22 (60%) የሆነው በጀት በኦዲቱ ሽፋን አግኝቷል፡፡ ይህም በቁጥር ያለውን ዝቅተኛ ሽፋን በማካካስ በአንጻራዊ ሁኔታ ከፍተኛ በጀት ያላቸውን ተቋማት በኦዲቱ ለመሸፈን ጥረት የተደረገበት ነው፡፡
4. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የኦዲት ስራውም ዓለም አቀፍና ብሔራዊ የኦዲት አሰራር መርሆዎችንና ስታንዳርዶችን ተከተለ ሆኖ ግኝቶቹም አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎች የተገኙባቸው ናቸው፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

ከዚህ ቀጥሎ በፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት የተደረሰበት የኦዲት አስተያየትና መልስ አሰጣጥ እንዲሁም ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችን አቀርባለሁ፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን ይህ አጭር ሪፖርት ከተወሰደበት አጠቃላይ ዘገባ አባሪዎች መመልከት የሚቻል መሆኑን ከወዲሁ መግለጽ እወዳለሁ፡፡

መ/ቤቱ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ግድፈቶች እንዲሁም አፈፃፀማቸው ደንብና መመሪያን ያልጠበቁ የተለያዩ ግኝቶች ያጋጠሙ ቢሆንም በዚህ ሪፖርት የተካተቱት ለም/ቤቱ ሪፖርት ሊደረጉ የሚገባቸው አንኳር አንኳር ግኝቶች ብቻ ናቸው፡፡

**የኦዲት አስተያየት**

5. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተ□ረጉ 152 መ/ቤቶች ውስጥ ለ133 (88%) **ከዚህ በስተቀር**፣ ለ6 (4%) **አስተያየት መስጠት አልተቻለም**፣ ለ2(1%) **አጥጋቢ አይደለም** የሚል አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ሌሎቹ 10(6%) የልዩ ኦዲት ሥራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት የማይጠበቅባቸው፣1(1%) የጭልጋ ወረዳ ገንዘብና ኢኮ/ል ጽ/ቤት የሰነድ ክፍልና ተያያዥ ክፍሎች ላይ ቃጠሎ በመከሰቱና ማስረጃዎች ለኦዲት መቅረብ ባለመቻሉ የኦዲት ሥራው የተቋረጠበት ነው፡፡
6. ከ152 መ/ቤቶች ውስጥ 6(4%) መ/ቤቶች የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና ስለ ሂሳቡ ትክክለኛ መሆን አለመሆን የሙያ አስተያየት ለመስጠት ባለመቻሉ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ ‹‹**አስተያየት መስጠት አልተቻለም**›› የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ መ/ቤቶችም፡-
    1. ወልዲያ ሆስፒታል
    2. ቦሩ ሜዳ ሆስፒታል
    3. አንዳሳ ዶሮ ብዜት ማዕከል
    4. ሃብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ደ/ሰ/ማዕከል
    5. ገንዳዉሃ ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
    6. መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸዉ፡፡
7. ከ152 መ/ቤቶች ውስጥ"**አጥጋቢ አይደለም**" የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው 2/1%/ መ/ቤቶች ሲሆኑ ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶችም፣
    1. ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
    2. እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸዉ፡፡

"**አጥጋቢ አይደለም**" □ሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት /ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፣የማጭበርበር ተግባር የተፈፀመባቸው፣ ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡

8. ከዚህ ውጭ ያሉት 133(88%) መ/ቤቶች በአንፃራዊ መልኩ በሪፖርቱ ውስጥ ጉልህ ቢሆኑም መሠረታዊ ያልሆኑና ተለይተው ከተገለፁት ግኝቶች በስተቀር በተነፃፃሪ የተሻለ የሂሣብ አያያዝና የመንግስት ገንዘብ አስተዳደር የታየባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2005/06 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር **"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** እና **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው በ4% መቀነሱ እና **"ከዚህ በስተቀር"** የሚለው አስተያየት በ6% መጨመሩ እንዲሁም አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ በ2% መቀነሱ የሂሣብ አያያዝ ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያመላክት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

**የኦዲት ሪፖርቶች መልስ አሰጣጥ፣**

1. የ2005 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ከመጋቢት/2005 እስከ ታህሳስ /2006 በኢንትሪም ኦዲት አካሄድ መሠረት በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉ 142 መ/ቤቶች መካከል 31(22%) እና በልዩ ኦዲት ከተከናወኑ 10 መ/ቤቶች መካከል 6 /60%/ መልስ ያልሰጡ ሲሆኑ ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 113 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 13 (12%) ስለሆኑ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል ያልታየበትና ለልዩ ኦዲት ሪፖርቶችም ምላሽ የመስጠት ዝግጁነቱ አናሳና አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡

10. **የ2005 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች** ውስጥ መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡-

**የክልል ማዕከል መ/ቤቶች**

1. ዱርቤቴ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ
2. አማኑኤል ቴክኒክና ሙያ ተቋም /ማቻከል/
3. ጎንደር የክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል
4. ሲሪንቃ ግብርና ኮሌጅ

**ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር**

5. ደጋ ዳሞት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
6. ቡሬ ወረዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
7. ሰሜን አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
8. ግሽ አባይ ጤና ጣቢያ

**ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳር**

9 እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
10 ሁለት እጁ እነሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
11 ደብረ ኤልያስ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ሰሜን ጉንደር ዞን አስተዳደር**

12 ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
13 ታች አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
14 አዲአርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
15 አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
16 ጠለምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር**

17 እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር**

18 ጉባላፍቶ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር**

19 ሐይቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
20 ተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
21 ደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት

**ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳዳር**

22 ጣርማበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
23 ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
24 መረሃቤቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
25 ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
26 መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል

**አዊ ብሄረሰብ**

27 ባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት
28 ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
29 ዳንግላ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት
30 ቻግኒ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት

**ኦሮሞ ብሄረሰብ**

31 ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸው፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤**

11. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት መካከል 59(42%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ሲሆን ለዚህም ዝርዝር ምክንያቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡-
    - የተሟላ የሂሳብ መዝገብ /ሌጀር/ ተዘጋጅቶ የሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገና ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ ሂሳብ የማያመለክት መሆኑ፣
    - በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና እንደጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላና ህጋዊ ቆጠራ ባለመደረጉ፤
    - ገንዘቡ በአንድ ገንዘብ ያዥ ተይዞ እየተዳደረ ባለበት ሁኔታ የውስጥ ገቢን ሳይጨምር የመደበኛ ጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ብቻ ነጥሎ ቆጠራ የሚደረግ መሆኑ፤
    - በገንዘብ ያዥ የሥራ መደብ ላይ በርካታ ሠራተኞች እየተለዋወጡ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን ያንቀሳቀሱ ሲሆን ርክክብ በተፈፀመበት ወቅት በገቢ ደረሰኞች፤ በወጪ ቫውቸሮችና በጥሬ ገንዘብ መከታተያ ሌጀሮች ላይ ርክክብ በተደረገበት እለት በጋራ በመፈራረም የመለያ /Cut-off/ ምልክት ያልተደረገ መሆኑ እና ገንዘብ ያዦች በሚቀያየሩበት ወቅት ርክክብ ሲፈፀም የጥሬ ገንዘብ ሌጀር የሚያሳየው ከወጪ ቀሪ በቆጠራ እየተረጋገጠ ርክክብ የማይፈፀም መሆኑ፣
    - ኦዲት አስደራጊዎች በኦዲት ወቅት የገቢና የወጪ ሂሣቡን መዝግበው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ምዝገባውን አጠናቀው ለማቅረብ አለመቻላቸው፣
    - የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሣቦች ከወጪ ቀሪያቸውን የሚያሣይ መቆጣጠሪያ የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው ሆኖ መገኘቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ በማመዛዘን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻሉባቸው ስለሆኑ መ/ቤቶቹ አሰራራቸውን በማረምና በየጊዜውም በውስጥ ኦዲተሮቻቸው እየተከታተሉ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደራቸውን እንዲያሻሽሉና ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ እንዲያረጋግጡ በየሪፖርቱ አሳስበናል፡፡

12. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 86,480.14 ከገንዘብ ያዦች በጉድለት የተገኘ ሲሆን በአጉዳዮች ላይ ክትትል ተደርጐ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡ ጉድለት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ከፍተኛውን ድርሻ ብር 84,157.85 የያዘው የሃብሩ ከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ሲሆን ለቶትለት መከሰት ዋና ዋና ምክንያቶች፤

የዕለት ከዕለት ቁጥጥርና ክትትል ካለማድረግ ጉድለቱ የተፈጠረ ሲሆን ይኸውም የጽ/ቤቱ የውሐ ቢል ሽያጭ ሠራተኛ የነበሩት ሥራ ከጀመሩበት ከጥቅምት/2004 ስራ እስካስረከቡበት ታህሳስ/2006 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ በልዩ ኦዲት ተሰርቶ ሲመዛዘን በጉድለት የተገኘ ነው፡፡

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት ከወጪ ቀሪ እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ9 መ/ቤት ብር 6,569,977.39 የሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ9 መ/ቤቶች ብር 1,336,445.01 የሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ (የጥሬ ገንዘብ በመብለጥ) የተስተዋለ ሲሆን ይኸው በውስጥ ኦዲተሮች እየተጣራ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

## ☐፹. ሂሣብ ኦዲት ውጤት፣

## 13. የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ገቢና ዘዴዎቹ፣

የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት አላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በ2005/06 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ3 መ/ቤቶች ብር 86,367.38 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ከመ/ቤቶች መካከልም፡-

- የፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 38,687.58 አንድ የወረዳው ገንዘብና ኢኮ/ል/ጽቤት ሂሣብ ኦፊሰር ሆነው እየሠሩ የነበሩ በተጨማሪነት ከ28/08/03—14/08/05 ዓ.ም የተዘዋዋሪ ብድርና ግብዓት ሽያጭ እየሠበሰቡ ወደ ባንክ እንዲያስገቡ ተወክለው በሠሩበት ወቅት ያለው ገቢና ወደ ባንክ ፈሰስ ያደረጉት ወጪ ሲመዛዘን በጉድለት መገኘቱ፤
- የደሴ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 26,510.00 የተሰበሰበው ገንዘብ በገቢ ማጠቃለያ መ/ሂ-65 ተጠቃሎ ለሂሣብ ክፍል ሣይቀርብ በተጭበረበረ የክፍያ ሂሳብ ማጠቃለያ ንዑስ የሥራ ሂደት ተወካይና የሥራ ሂደቱ አስተባባሪ በሆኑት ባለሙያ ፊርማና ቲተር አስመስሎ በመጠቀም እና ሃሰተኛውን የሂሳብ ማጠቃለያ (መ/ሂ-65) ቁጥር በደረሰኞች ጀርባ በማወራረስ ገንዘቡ ተጠቃሎ ፈሰስ እንደሆነ በማስመሰል ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ፤
- የጓንጓ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ል/ጽ/ቤት ረዳት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ብር 21,170.00 ገቢ በሚሰበስቡበት የገቢ ደረሰኝ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ በመሰረዝና በመደለዝ እንዲሁም በራሪውንና ቀሪውን በማበላለጥ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቻችን ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሳወቅን ሲሆን በጠቅላላው ከተጭበረበረው ገቢ ዉስጥ የፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ድርሻ ላይ ብር 37,377.00 ተመላሽ

መደረጉንና በቀሪው ገንዘብ ላይ በፍትህ አካላት ክትትል እየተደረገበት በክርክር ላይ ሲሆን ደሴ ዙሪያ ወረዳን በሚመለከት ጉዳዩ በቀጥታ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተላከ በመሆኑ የሚደረስበትን ውሳኔ በግብረ-መልስ ወደፊት የሚታወቅ ይሆናል።

## ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ፤

14. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉ 142 መ/ቤቶች □ስዓ በ48 መ/ቤቶች ብር **26,199,992.39** ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት ቒ. በ□ቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል። ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግሥት ገቢ ከሚታይባቸው የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤቶች መካከል የደሴ ከተማ አስተዳደር ብር 19,078,848.55፤ የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር` ብር 3,838,272.81፣ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ብር 990,673.89፤የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር አስተዳደር ብር 530,434.47፤ የደባርቅ ከተማ አስተዳደር ብር 510,534.47 እና የከምሴ ከተማ አስተዳደር ብር 390,698.51 ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ።

ስለሆነም ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ያሳሰብን ሲሆን ጽ/ቤቶቹ ውዝፍ ገቢውን ለመሰብሰብ ጥረት እንደሚያደርጉ በመግለጽ ምላሽ ከመስጠት በስተቀር በገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደተሰበሰበ በግብረ-መልሶቻቸው አላመላከቱም። መንግሥት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን ከተሰጣቸው መ/ቤቶች ሊሰበሰብ የታቀደውን በታሳቢነት በመያዝ መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም በገቢ አሰባሰብ ላይ መንግሥት ያደረጋቸውን የግብር ስርዓትና የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት ሁለንተናዊ ማሻሻያዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ገቢን በወቅቱ ለመሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየጽ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት አሳስበናል።

## ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፣

15. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ28(18%) መ/ቤቶች ብር 2,849,521.79 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም።

የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም፤

- ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 667,947.86፣ የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤
- ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ብር 617,617.50 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤
- መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 345,434.17 የያዙ ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤
- ከለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 216,798.93 (በናሙና ከተመረጡ የመደበኛ ገቢ እና የስፖርት ምክር ቤት) የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤
- ማቻከል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 140,000.00 (የስፖርት ምክር ቤት ገቢ መሰብሰቢያ) የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፤
- የታች ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 136,357.49 የያዙ (የስፖርት ምክር ቤት፤ የእንስሳት ጤና ኬላዎች፤በንግድ ትራንስፖርት ጽ/ቤትና ከአዳጊ ጤና ጣቢያዎች) ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፤

- ለጋምቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 104,090.00 የያዙ (የስፖርት ምክር ቤት) ደረሰኞች ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ሲሆን በኦዲት ወቅት እንዲቀርቡ ተፈልገው አልተገኙም፡፡

ይህም ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ በኦዲት ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ደረሰኞቹ ቀርበው የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ለኦዲት ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም ደረሰኙ ስለመቅረቡም ሆነ የገቢው ትክክለኛነት ስለመረጋገጡ በአጠቃላይም ስለተወሰደው እርምጃ በምላሹ አልተመላከተም፡፡

## □ወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፣

### የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣

16.በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ8(5%) መ/ቤቶች የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ብር 1,292,111.01 ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችም፡-

**የጠለምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

16.1. በወረዳው በተለያዩ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው የሚሠሩ 6 ባለሙያዎች በድምሩ ብር 146,316.73 ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ከተከፈለው ደመወዝ በላይ በብልጫ እንዲፀድቅ በማድረግ ልዩነቱን ለግል ጥቅም ያዋሉ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ለፍትህ አካላት በሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት በጉዳዩ ላይ ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ እንደሆነ ከተገኘው ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

**የሀብሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

16.2. በወረዳው በተለያዩ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው የሚሠሩ 4 የተለያዩ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በድምሩ ብር 95,471.65 ከተለያዩ የመደበኛና የእርዳታ ሂሳቦች በተመሳሳይ ቀናት በተደጋጋሚ ጊዜ በዓመት ካሉት 365 ቀናት በላይ እስከ 567 ቀናት የውሎ አበል በመውሰድ ለግል ጥቅማቸው አውለው መገኘታቸው በኦዲት ማስረጃ በመረጋገጡ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን ባሳሰብነው መሰረት በፍትህ አካላት በተደረገ ጥረት ገንዘቡ ሙሉ ለሙሉ ከየግለሰቦቹ ላይ መሰብሰቡን ከተገኘው ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

**የጐንጅ ቆለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

16.3. የግዥ ኦፊሰሮች እንዲሁም በወቅቱ የጽ/ቤቱ ኃላፊ የነበሩት ከእቃ አቅራቢ ጋር በመመሳጠር በ4 የተለያዩ ዓይነት ዕቃዎች (የተለያዩ ኘሪንተርና የፎቶ ኮፒ ማሽን) እያንዳንዱን በብር 20.00 ለማቅረብ በጨረታ ሰነድ ላይ በመሙላት ሆን ብሎ ከገበያ ዋጋ በታች እጅግ በወረደ ዋጋ በመወዳደር እና በሌሎች መ/ቤቶቹ በብዛት በሚገዟቸው የቢሮ እቃዎች፣የጽህፈት መሳሪያና የጽዳት እቃዎች ወዘተ ደግሞ ከፍ ያለ ዋጋ በጨረታ ሰነድ ላይ በመሙላት ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ በጥቅል ድምር ውጤት በጠቅላላ የግዥ

መጠን ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያለው እቃ ለማቅረብ የጨረታ አሸናፊ እንዲሆኑ የተደረገና ግዥው በየእቃዎቹ ዓይነት ወይም በሎት ተከፋፍሎ ቢወዳደሩ ኖሮ የብር 203,891.65 ቅናሽ ማግኘት እየተቻለ ኢፍትሃዊ በሆነ ውድድር አላግባብ በተጋነነ ዋጋ እንዲያሸንፍ ከተደረገና ውል ከተያዘ በኋላ ዋጋቸው ዝቅ ብሎ የተሞሉ ማሽኖችን ያላካተተ ከፊል ግዥ እንዲገዛ የተደረገ የግዥ ሂሣብ ነው፡፡

አቅራቢው ጨረታውን ለማሸነፍ አስቦና ሆን ብሎ የፕሪንተርና ፎቶ ኮፒ ማሽኖችን ዋጋ አሳንሶ ከተወዳደረና የግዥ ኦፊሰሮችና የጽ/ቤት ሃላፊው ይህንኑ እያወቁ አላግባብ በጥቅል ዋጋ እንዲያሸንፍ ካደረጉ በኋላ በከፊል ግዥ ያቀረቧቸው እቃዎች ዋጋ ከተዋዳደሪ አቅራቢዎች ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከፍ ያለ ልዩነት ያለው መሆኑ ተደርሶበታል፡፡

ይህንኑ የማጭበርበርና ኢፍትሃዊ ውድድር በፈጸሙ ላይ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለፍትህ አካላት በተላለፈው ሪፖርት መነሻነት በፍትህ ቢሮ በኩል ተጨማሪ ማስረጃዎች ተጠይቀው ተፈላጊ ማስረጃዎች የተሰበሰቡ በመሆኑ ለቢሮው የሚላኩ ሲሆን በስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በኩል ጉዳዩ በባለሙያ ምርመራ ላይ መሆኑ በላኳቸው ግብረ መልሶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

16.4. የወረዳዉ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ሁለት ሾፌሮች ከባቲ ከተማ ዉጭ መስክ ተሰማርተዉ እያለ ባቲ ከተማ እንደነበሩ በማስመሰልና መስክ ከሄዱበት አቅጣጫ ውጭ በሚገኙ ከተሞች ነዳጅና ቅባት እንዲሁም የመኪና እጥበትና የጎማ ጥገና ግዥ በሚል በድምሩ ብር 48,503.84 በተጭበረበረ ማስረጃ ሂሳቡ ተወራርዶና ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ በኦዲት በመረጋገጡ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን ባሳሰብነው መሰረት በጉዳዩ ላይ ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ እንደሆነ ከፍትህ አካላት ከተገኘ ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

## የሰቆጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

16.5. ለስራ ተቋራጭ ተወካይ ክፍያ ሲፈጸም በግንባታ ቦታ ላይ የቀረበው የግንባታ ዕቃ መጠን (ማቴሪያል ኦን ሳይት) ብር 266,639.38 ሆኖ እያለ በክፍያ የምስክር ወረቀቱ ላይ ሲተላለፍ ብር 280,305.68 በመሆኑ ልዩነት ብር 13,666.30 ለተቋራጩ ተወካይ በብልጫ ተከፍሎና በወጪ ፀድቆ የተገኘ መሆኑ በመረጋገጡ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት በጉዳዩ ላይ ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ እንደሆነ ከፍትህ አካላት ከተገኘ ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

## የማቻከል ወረዳ ውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት

16.6. የወረዳው ውሃ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊና የፕሮጀክቱ አስተባባሪ፡-

- በግንባታ የጥራት መጓደል ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ ለሆኑት 8 የውሃ ጉድጓድ የተከፈለ ብር 258,939.03፣
- ግንባታው ለመሰራቱ በሚመለከተው የምህንዲስና ባለሙያ ሳይረጋገጥ ለ9 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ በሚል ተከፍሎ የተገኘ ብር 45,853.57፣

- የ7 ውሃ ተቋማት ግንባታቸው ከተጠናቀቁ /ከተቋረጡ/ በኋላ ቀሪው ገንዘብ ብር 12,919.34 ተመላሽ መሆን ሲገባው ከመመሪያ ውጪ በቀበሌ የውሃ ኮሚቴዎች እጅ እንዲቀመጥ መደረጉ ለብክነት በር ከፋች ሆኖ በመገኘቱ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለፍትህ አካላት ባሳሰብነው መሰረት የፍትህ አካላት ጉዳዩን ላይ ክስ ለመመስረት እየመረመሩት እንደሆነ በሰጡት ግብረ መልስ አሳውቀዋል፡፡

**ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤**

17. በ22 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,427,736.58 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብና ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተከፈለዉ ደግሞ ታክሱ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ የሚያስገድድ የመቆጣጣሪያ ስልት ስለሌለና ሊሰበሰብ ስለማይችል አፈፃፀሙ የመግስትን ገንዘብ በማጭበርበር ከተጠቃሚው (ከከፋዩ) በመንግስት ስም ሰብስቦ ለግል ጥቅም በማዋል እንዲሁም በሌሎች ዜጎች ላይ ኢ-ፍትሐዊ የገበያ ውድድር በመፍጠር በደል የሚያደርስ በመሆኑ ላለፈው ትኩረት በመስጠት እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ተጨማሪ እሴት ታክስን ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

**አላ□ባብ □ተ□ናመ □እጸ፣**

18. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ106(70%) መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር **8,628,883.49** አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 100,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- በጤና ጥበቃ ቢሮ ለደልጊ፣ለአይከል፣ለፈረስ ቤት፣ለጉሀላ፣ለቻግኒ፣ለደነባ፣ለቡሬና ለሸዋሮቢት ሆስፒታሎች እንዲሁም ለመቄት ወረዳ ጠጅ ሳር፣ለላይ ጋይንት ወረዳ ሰጥላ፣ለሰቆጣ፣ለክርስቶስ ሰምራ ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎች ግንባታ ሲከናወን በውለታ ከተያዘው የገንዘብ መጠን በላይ በሂሳብ ስህተት ምክንያት በድምሩ ብር 234,666.17 በብልጫ ያላግባብ ለተቋራጮች ተከፍሎ በመገኘቱ ገንዘቡ ከየሚመለከታቸው አካላት እንዲመለስ ያሳሰብን ሲሆን በቢሮው በኩል በ2006 በጀት ዓመት ቀሪ ክፍያ ሲፈፀም የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል የሚል ምላሽ ሠጥቷል፡፡
- ውሃ ሃብት ልማት ቢሮ የአንጀብ አንስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የ9ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በስሌት ስህተት የተነሳ የጥራት አፈጻጸም ዋስትና መያዥያ ብር 821,388.36 በድጋሜ በአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ስም በወጭ ተመዝግቦ መገኘቱና ለሚሊኒየም ዲቪሎፕመንት ጎል (MDG) የ12 ወረዳዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ ግንባታ የዲዛይን ጥናት ለሰራው ለአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ ብር 20,457.50 በብልጫ ተከፍሎ በመገኘቱ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን ባሳሰብነው መሰረት ለድርጅቱ ከሚከፈለው ቀጣይ ክፍያ ላይ ተቀንሶ የቀረ መሆኑ እና ቀሪው ብር ደግሞ የማስተካከያ ምዝገባ ማድረጉን ቢሮው በግበረ መልሱ አሳውቋል፡፡

- ትምህርት ቢሮ በደቡብ ጎንደር ዞን የላይ ጋይንት ወረዳ የጥጥራ፣ በደቡብ ወሎ ዞን መቅደላ ወረዳ የደደሪ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረብርሃን ከተማ ቀበሌ 08 ጩርቆስ ማደሪያ፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ከተማ ለወንጌባ፤ በደጋ ዳሞት ወረዳ ለፈንቲካ፣ በደቡብ ጎንደር ዞን በምዕራብ እስቴ ወረዳ ለዋላዩ፣ በዋግምራ ዞን በሰቆጣ ከተማ ለቲያ፣በዳህና ወረዳ ለጭርቁዘና፣ በአዊ ዞን ቻግኒ ከተማ ለወልድሀይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በውለታው መሰረት የተከናወነው የስራ ልኬታ መጠን (ቴክ ኦፍ ሽት) ወደ ክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በትክክል መተላለፍና ክፍያ በዚህ መሰረት መፈፀም ሲገባው በብልጫ እንዲተላለፍ በመደረጉ ያለአግባቡ ብር 251,509.41 ለተቋራጮች ተከፍሎ የተገኘ ሲሆን ቢሮውም ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ለሚመለከታቸው በደብዳቤ አሳውቆ በመከታተል ላይ የሚገኝ መሆኑን በግብረ መልስ ገልቷል፡፡
- የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፣

- የአምደ ወርቅና የአንበሳሜ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ግንባታ ውል ላይ የተጠቀሰው የዋጋ ቅናሽ በድምሩ ብር 337,289.59 ክፍያ ሲፈፀም ሳይቀነስ መሰጠቱ፣
  - የቢሮው ህንፃ ግንባታ 6ኛና 7ኛ ክፍያ፤ የዳባት እና የአንበሳሜ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ግንባታ በሥራ ዝርዝሩ ላይ የቀረበው ወደ ማጠቃለያ ሲተላለፍ በድምሩ ብር 22,862.87 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፣
    - ጎንደርና ወልዲያ ከተማ ለተዘጋጁ ስልጠናዎች ሰልጣኞች በቆዩበት ከተማ የውሎ አበል ታሪፍ መሰረት ባለመከፈሉ በሥራ ቦታቸው እያሉ በከተማ ውስጥ ለተሰጠ ስልጠናና በስልጠናው መገኘታቸው በስዓት ፊርማ ላይ ሳይፈርሙ በድምሩ ብር 11,642.00 በብልጫ የውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
  - ምዕራብ ጐጃም ዞን ገ/ኢ/ል/መምሪያ ብር 1,263,917.75፣ የአስተዳደር ጽ/ቤት፣ አዳራሽ፣ መጋዘን፣ አጥርና የጥበቃ ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ከሥራ ዝርዝር ወደ ክፍያ ማጠቃለያ ሲተላለፍ እና የኘሪንተር ግዥ ሲፈፀም በድምሩ ብር 1,263,917.75 አላግባብ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
  - ሁለት እጅ እነሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በቀራኒዎ ከተማ ለተሰራ ኮንቲነር ሼድ የቆርቆሮ ማገር 7 በ15 ሴ.ሜ በሆን ዝግባ እንጨት ለመስራት ውለታ ተይዞ እያለ በባህር ዛፍ እንጨት ተሰርቶ ሲቀርብ የግንባታ ክትትል ባለሙያው ሥራው በሥራ ዝርዝሩ መሰረት በዝግባ እንጨት እንደተሰራ አስመስሎ በማረጋገጡ ብር 2,739,906.00 ለተቋራጩ አላግባብ ክፍያ ተፈፅሞ በመገኘቱ በወቅቱ የነበረው የባህር ዛፍ ዋጋ ተጠንቶና ተቀንሶ ልዩነቱ ለመንግስት ተመላሽ እንዲደረግና ሆን ብለው ስህተት በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፣
  - ጐንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በአዳማና ጐንደር ለተካሄደ ስልጠና አበልና ለ4ኛው የከተሞች ቀን የነዳጅ ግዥ ሲፈፀም ብር 41,701.18 በብልጫ መከፈልና ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች በሥራ ቦታቸው እያሉ በተመሣሣይ ቀን በድጋሚ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 77,265.90 በድምሩ ብር 118,967.08 ተከፍሎ መገኘቱ፣
  - የእብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 200,000፣ የአጃ ዘቀል ሞቃ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጽሐፍትና ቤተ ሙከራ ግንባታ ህንፃ ተቋራጩ በገቡት ውል መሰረት ስራውን እንዲያጠናቅቁ ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ ተቋራጩ አስቀድመው የወሰዱትን ብር 106,000.00 በቅድሚያ ለወሰዱት ክፍያ በሥራ ሳያወራርዱና ለተቋራጩ የተሰጠው የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ ካለፈ በኂላ ቀኖችን በመሰረዝ

በመደለዝ የቅድሚያ ክፍያ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የተከፈለ በማስመሰል ማዘጋጀታቸውና በተጨማሪም ተቋራጩ የገንዘብ እጥረት ስለገጠማቸው በሚል ምክንያት ያለፈውን የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ሳያወራርዱና ሥራውንም በውለታው መሰረት ሳያጠናቅቁ ተጨማሪ ቅድሚ ክፍያ ብር 94,000.00 በድምሩ ብር 200,000.00 ያለአግባብ የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንዲከፈል ተደርጓል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ወጭ እስከ ሆነበት መጋቢት 26/2006 ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታውን ሳያጠናቅቁ ቆይተው ስራውን አቋርጠዋል፡፡

ስለሆነም በወቅቱ የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ የተሰጣቸውን የህዝብና የመንግስት ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው የመንግስት ገንዘብ ባክኖ እንዲቀር በር በመክፈታቸው በህግ እንዲጠየቁ እና የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባር በመፈጸም ያለስራ የመንግስት ገንዘብ ወስደው ስራውን ካቋረጡት ተቋራጭ ላይ ገንዘቡ እንዲመለስ ሆኖ በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ለፍትህ አካላት ሪፖርት የተላለፈ ሲሆን በህግ ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ እንደሆነ በግብረ መልሳቸው አሳውቀዋል፡፡

- በዋድላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ለኮን ብሩህ ተስፋ ስታዲየምና የአትሌትክስ መንደር ዙሪያ አጥር ግንባታ ሣይከናወን ብር 139331.94፤ እንዲሁም ለስልጠና፤ ለውሎ አበልና ለነዳጅ ግዥ ብር 87,911.94 አላግባብ በብልጫ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

- በተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች በመደበኛ ሥራ ገበታቸው እያሉ ከተማ ላይ ለተሰጠ ስልጠና፣በተመሳሳይ ቀን በድጋሚ፣መስክ ሳይሄዱ የተከፈለ ውሎ አበልና የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች የቢላ ጤና ጣቢያ መፀዳጃ ቤት እና ለኮሎገነት ጤና ጣቢያ የቆሻሻ መቅበሪያ ጉድጓድ ግንባታ ክፍያ በድምሩ ብር 127,565.56 አላግባብና በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
  በየሪፖርቶቻችንም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለፍትህ አካላት ባሳሰብነው መሰረት ገንዘቡ ተመላሽ እየተደረገ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡
- በመንዝ ማማ ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የሞላሌ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተጨማሪ የመማሪያ ክፍል ግንባታ ከተያዘው ውል በላይ ብር 128,275.81 ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉና ለስልጠና ላልተሳተፉ የግብርና ልማት ጣቢያ ሰራተኞች መስክ ከሄዱበት ከተማ የውሎ አበል ታሪፍ በላይ ብር 1,464.70 በድምሩ ብር 129,740.51 ተከፍሎ መገኘቱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

## የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

19.ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ27 (18%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 19,007,315.58 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- በአለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የግብርና ጽ/ቤት በጋራስጌ፣በወኪና፣ በሻሁራ ላስገነባቸው የእንስሳት ህክምና በረት በድምሩ ብር 37,324.00 የግንባታ የክፍያ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብና የሻሁራ ቴክኒክና ሙያ

ተቋም፣በአምቻሆና በአቱጋ ቀበሌ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ክፍያ በድምሩ ብር 1,676,200.12 ዝርዝር የስራ ስፍር ልኬት ሳይቀርብ በአጠቃላይ ብር 1,713,524.12 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፤

- በሞጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በከተማው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሥራ በትክክል ለመሠራቱ የሥራ ዝርዝር ሳይቀርብና መሰራቱ ሳይረጋገጥ (ከመሠራቱ በፊት) ብር 2,802,487.95 ተከፍሎ ተገኝቷል፤
- በምዕራብ ጐጃም ዞን ገ/ኢ/ል/መምሪያ የአስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ፣ አድራሻ፣ መጋዘን፣ አጥርና የጥበቃ ቤት ግንባታ ለደረቋ ቀበሌ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ግንባታ መጀመሪያ ዙር ክፍያ በድምሩ ብር 1,152,100.55 ክፍያ ሲፈፀም የግንባታ ሥራ ዝርዝር ሣይቀርብ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፣
- የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በድምሩ ብር 8,345,188.00፣
  - የቢሮው ግንባታ ፕላንና ውል ላይ ያልተካተቱ የሳይት፣የአጥር፣ የጥበቃ ቤት እና አሳንሱር አቅርቦትና ገጠማ ሥራዎች ጨረታ ወጥቶ መሰራት ሲገባው ያለምንም ጨረታ የብር 4,840,480.16 ተጨማሪ ሥራ ተብሎ በመሰጠቱ መንግስት ከጨረታ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም እንዲቀር መደረጉ፣

- ለቢሮው ግንባታ ለሥራ ጥራት አፈጻጸም ዋስትና መያዥያ 5% ተቀንስ መያዝ ሲገባው የ6ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፅም ሙሉ ለሙሉ ግንባታው ሳይጠናቀቅና የመጀመሪያ ርክክብ ሳይፈፀም 2.5% ብቻ እንዲቀንስ በመደረጉ ግማሹ ብር 401,856.90 እና የ7ኛ ዙር ክፍያ የዋስትና መያዣ ሂሳብ ሳይቀነስ ብር 28,402.57 በድምሩ ብር 430,259.41 የግንባታ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፤
  - የምስራቅ በለሳ፣ የሳይንት አጅባርና የአምደወርቅ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ግንባታ ሥራ በድምሩ ብር 3,074,448.38 የግንባታ ሥራ ዝርዝር ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

በእነዚህ ግኝቶች መሠረት ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንዲስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል።

## ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፣

20. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ በኦዲት ወቅት ተጠይቀው በ12(8%) መ/ቤቶች ብር 13,845,728.41 የተገኘ ሲሆን ከመ/ቤቶች መካከልም:-

- በደብረ ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 6,854,975.10 ለተሸከርካሪ ግዥ ለነዳጅና ቅባት፣ለግለሰቦች የካሳ ክፍያ፣ለመሰረተ ልማት ግንባታና ለህንፃ ግንባታ ሥራ የተከፈለባቸው፣ በዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,999,086.11 ለትምህርት ጥራት ማስፈፀሚያ ለየወረዳዎች የተላከበት ማስረጃ፣ በጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 663,631.45፣በፍኖተ ሠላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የ2002 በጀት ዓመት ብር 177,239.54፣በጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 429,736.35፤ የደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 323,195.69፤የወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,022,224.25 ለተሸከርካሪ እድሳትና ጥገና፣ለህንፃ ግንባታ፣ለአላቂና ቋሚ የቢሮ ዕቃዎች ግዥ እንደዋለ የተመለከተ ሂሳብ በድምሩ ብር 13,845,728.49 የያዙ የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪዎቹን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም።

ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ወንጀል መዋል አለመዋላቸው በኦዲት ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ማስጃዎች ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ ይሁንና ስለተወሰደው እርምጃ የተሰጠ ግብረ መልስ የለም፡፡

## የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሣብ፤

21. ክቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለ ዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ118 (78%) መ/ቤቶች ብር 107,343,734.23 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ የግዥ አፈጻፀም ጉድለት ጎልቶ የሚታይባቸውና ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ ግኝት የተስተዋለባቸውን መ/ቤቶች ብንመለከት፡-

- የጐንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 29,093,944.80 ልዩ ልዩ የግንባታ ዕቃዎች፣ የመኪና መለዋወጫ ዕቃና የጽ/መሣሪያ ግዥ እንዲሁም ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ካላሳደሱ አቅረቢዎች የተፈፀመ ግዥ፤
- የፍኖተ ሠላም ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ብር 3,211,127.58 እና የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 7,545,714.52 የኮበል እስቶን ድንጋይ እና የጠጠር ግዥ፤ የኮበል ስቶን ንጣፍ ሥራ፣
- የላሊበላ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 7,964,284.41 የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች ፣ለማጓጓዥያ ፣ ለማሽነሪ ክራይ፣ለኮበል ስቶን ንጣፍ ሥራና የደንብ ልብስ ግዥዎች፣
- የወልዲያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 6,521,054.05 ለተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች ፣ለማሽነሪ ክራይ ለልዩ ልዩ ደረሰኞችና የጽ/መሳሪያ ግዥ፣
- የዋድላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ፣ስ/ማዕከል ብር 5,973,055 ለኮን ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ግንባታና ለአሞቡላንስ ጥገና ሥራ ላይ የዋለ የአገልግሎት ግዥ፣
- ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,082,576.94 የተሽከርካሪ መኪና መለዋወጫ ዕቃና ለላፕቶፕና ፕሪንተር ግዥ የዋለ ሂሳብ የግዥ ስርዓትን ያልጠበቀ ግዥ የተገኘባቸው ናቸው፡፡

  ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የዕቃ ግዥ መመሪያ በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2005 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 289,013,714.62 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ36 ሲጨምር በገንዘብ መጠን ግን በብር 181,669,980.39 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል ግዥ መፈጸም ላይ አሁንም ብዙ እንዳልተሸሻለ ያመለክታል፡፡

## የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፣

### *22.* የንብረት ሂሳብን ማመዛዘን ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በአብዛኞቹ የክልሉ መ/ቤቶች የሚታየው የንብረት አያያዝና አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት የመንግስት ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና ከዚያ ወዲህ ስለንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተሻሻሉ መመሪያዎች በሚያዙት መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ68(45%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቶቹ:-

- አላቂና ቋሚ ዕቃዎች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ እየተቆጠሩ በመከታተያ መዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከሩ በመሆኑ፣
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (የእቃ መቆጣጠሪያ ካርዶች) ባለመቋቋሙ እና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማይደረግ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም፤ የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤ አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ!**

**ማጠቃለያ፣**

**የኦዲት አስተያየትን በተመለከተ**

23. በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2005/06 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር **"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** እና **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው የኦዲት አስተያየት በ4% መቀነሱ እና **"ከዚህ በስተቀር"** የሚለው አስተያየት በ6% መጨመሩ እንዲሁም አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ በ2% መቀነሱ የሂሣብ አያያዝ ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያመላክት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡

**ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ**

24. በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉ 142 መ/ቤቶች 31 (22%) እና በልዩ ኦዲት ከተከናወኑት 10 መ/ቤቶች 6 (60%) መልስ ያልሰጡ ሲሆኑ ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 113 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 13(12%) ስለሆኑ የ2005 በጀት ዓመት መልስ አሰጣጥ ከ2004 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል ያልታየበትና ለልዩ ኦዲት ሪፖርቶችም ምላሽ የመስጠት ዝግጁነቱ አናሳና አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ፤**

25. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት መካከል 59(42%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ

ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ ይህም የተዘረጋውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አስተዳደር ስርዓት በመተግበር ረገድ በመ/ቤቶች ሰፊ ውስንነቶች ያሉ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**የገቢ ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ፤**

26. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉ 142 መ/ቤቶች ውስጥ በ48 መ/ቤቶች በሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት ገቢ በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ይህም መንግስት በዘመኑ በሚሰበስበው ገቢ ለመፈጸም ባቀዳቸው የፊዚካል ስራዎች ላይ ቀላል የማይባል አሉታዊ ተጽዕኖ □የሚያስከትል መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡

27. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ28(18%) መ/ቤቶች የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህም ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ በኦዲት ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የጣለና ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**የወጪ ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ፤**

28. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ8(5%) መ/ቤቶች የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ይህም የማጭበርበር ድርጊት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረቀቀና እየተወሳሰበ የመጣና ለዚህም የተጠናከረ የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል እና የፋይናንስ ተጠያቂነት ስርዓት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ ያሳያል፡፡

29. በመ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብና ገንዘቡ በወቅቱ ፈሰስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ ፈሰስ ሳይደረግ በስራ ተቋራጮች እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

30. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ106(70%) መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

31. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ በኦዲት ወቅት ተጠይቀው በ12(8%) መ/ቤቶች ለኦዲት ሊቀርቡ አለመቻላቸው በማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ድርጊት መዋል አለመዋላቸው በኦዲት ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

32. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ27 (18%) መ/ቤቶች ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

33. ክቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለ ዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች ቱሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ118 (78%) መ/ቤቶች ስዓ የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ግዥዎች ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

**የንብረት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ፡-**

34. ስለንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተሻሻሉ መመሪያዎች በሚያዙት መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት በ68(45%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብ አመዛዝኖ ጉድለት መኖር አለመኖሩን በኦዲት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፤**

በዚህ ዓመት በኦዲት ሪፖርቱ ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከዚህ በላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ አንፃር ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሐብት አመራር ስርዓት መጠናከር እንዲችል የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶች አቀርባለሁ፡፡

35. **አሁንም የኦዲት ተደራጊ ተቋማት የኦዲት አስተያየት መሻሻል ማሳየት የሚገባው መሆኑ፤**

በእርግጥም የኦዲት ተደራጊ ተቋማት የኦዲት አስተያየት መሻሻል ማሳየት የሚችለው በአጠቃላይ በፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ስርዓታችን ላይ በሚደረጉ ማሻሻያዎችና በሚገኙ ውጤቶች ቢሆንም ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት የተዘረጋውን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ስርዓትን በጥብቅ ዲሲፕሊን በመፈፀም ነቀፌታ የሌለው የኦዲት አስተያየት (ንፁህ የኦዲት አስተያየት) ማግኘት እንዲችሉ አቅደው መስራት ይገባቸዋል፡፡

36. **በኦዲት ስራ አመራር ሪፖርት መልስ አሰጣጥ ረገድ የሚስተዋለው ችግር ሙሉ በሙሉ መቀረፍ የሚገባው ስለመሆኑ፤**

በዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 21(3) መሰረት ከኦዲት ተደራጊ ተቋማት ግዴታዎች መካከል በሁሉም ኦዲት ተደራጊዎች መፈፀም የሚገባው በሪፖርቶች ላይ የተገለፁ ግኝቶችን አስመልክቶ በ15 ቀን ውስጥ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድና ይሄንኑ ለዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይሄንኑ ድንጋጌ ወደ ጎን በመተው በግኝቶች ላይ ም/ቤቱ በእርምጃ አወሳሰድ ማስረጃዎች ላይ ተመስርቶ በጥልቀት ከመምከርና አቅጣጫ ከማስቀመጥ አንፃር ገደብ የሚጥል በመሆኑና

ህግንም ማክበር ተቀዳሚ ግዴታ በመሆኑ ኦዲት ተደራጊዎች ሙሉ በሙሉ ከዚህ ችግር የሚወጡበትን አሰራርና አካሄድ ቀርፀው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

37. **የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ላይ ቁጥጥርን ማጠናከር በሚመለከት፤**

ከግኝቶች መረዳት እንደሚቻለው በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ ሲሆን ይህም የህዝብና የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና የተለያዩ ምዝበራዎች የሚያጋልጥ በመሆኑ በየተቋማቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡

38. **የመንግስት ተቋማት ከግብር ከፋዩ ተጨማሪ እሴት ታክስን ቀንሶ የማስቀረት አሰራርን እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ መዘርጋት አስፈላጊ ስለመሆኑ፤**

በዚህ ሪፖርታችን ተጨማሪ እሴት ታክስን በመንግስት ተቋማት ቀንሶ የማስቀረት አሰራር በሁሉም የመንግስት መዋቅር የአስተዳደር እርከኖች ባለመተግበሩ በተለይም በወረዳና በተመሳሳይ አደረጃጀት የሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች አካባቢ መጠኑ በሚሊዮን የሚቆጠር ተጨማሪ እሴት ታክስ ፈሰስ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ይሄንኑ አሰራር በታችኛው የመንግስት አስተዳደር እርከን ጭምር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

39. **የገቢና የወጪ ሂሳብ የማጭበርበሪያ ክፍተቶችን ማጥበብ የሚችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፤**

በሪፖርታችን ላይ በግልፅ እንደተመላከተው በገቢና ወጪ ሂሳቦች ላይ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የመንግስትን ገንዘብ ለግል ጥቅም የማዋል ሁኔታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ መልካቸውን እየቀየሩ ይሄዳሉ፡፡ ከአጠቃላይ ስራ አንፃር በረጅም ጊዜ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ለውጥ የሚፈቱ ችግሮች ቢሆኑም ጎን ለጎን ደግሞ ክፍተት የፈጠሩ አሰራሮችን እየፈተሹ በማስተካከል፤ የአመራሩንና የፈፃሚውን አቅም በመገንባት የመንግስትን ሃብት በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የፍትህ አካላትም የጀመሩትን ከኦዲት ተቋሙ ጋር በቅንጅት የመስራት አሰራር ይበልጥ በማጎልበት አጥፊዎች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

40. **የግንባታ አፈፃፀም እና ለዚሁ የሚፈፀመው ወጪ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያስፈልገው ስለመሆኑ፤**

በሪፖርታችን ላይ እንደተመላከተው የግንባታ ስራዎች አፈፃፀምና የወጪ አስተዳደር ስርዓቱ በርካታ ግድፈቶች ያሉበትና ያለአግባብ ተከፍለው የሚገኙ ወጪዎችም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ከመሆኑም በላይ በግንባታ ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በዘርፉ አሁን ላይ የጀመሩትን የመቆጣጠር ኃላፊነት ይበልጥ በማጠናከር ከችግሩ መውጣት ይገባል፡፡

41. **የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤**

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሰራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወነ ከመዝገቡ ከወጪ ቀሪ ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን ማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

42. **በየደረጃው የሚገኙ የህዝብ ምክር ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፤**

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጭ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በተለያዩ የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች (በተለይም በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ) አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባዔ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሊ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

**ደሴ ጥላሁን አያሌው**

**ዋና ኦዲተር**

**ጥቅምት /2007**

**ባህር ዳር**